ቁጥር 2

በውስጥ ገጾች

- ✓ ቀዳሚ ነገር
- ✓ ዳግማዊት ማርያም ?
- ✓ ጎረቤቶቻችን ምን እያደረጉ ነው ?

በሚቀጥለው እትም

- «አንተ ለዘለዓለም ካህን ነህ »
- ክርስቶስን የማያውቁ ክርስቲያኖች

ኪዳነ ምህረት :- የምህረት ውል ወይም ስምምነት ማለት ነው:: እኛ ከእግዚአብሔር ዘንድ ዘላለማዊ ምህረት እንድናገኝ የረዳን የክርሰቶስ ስም ነው:: የምህረትን ኪዳን ያገኘነው በእርሱ ነውና::

Scanned by CamScanner

ቀዳሚ ነገር

መንፈሳዊ አባቶች ለመንፈሳዊ ልጆቻቸው እነርሱም ለልጆቻቸው እያለ አሁን እኛ ያለንበት ዘንድ ለመንፈሳዊው ሕይወት መመሪያ መተዳደሪያ ይሆነን ዘንድ ቅዱሱን መጽሐፍ በብዙ ተጋድሎና ሰማዕትነት እንዲደርስ አደረጉ። እኛ ጋር ሲደርስ ግን ያ! የተከፈለለት ሰማዕትነት ሁሉ ተረስቶ ማንም እንደፈለገ የሚያጣምመው እንደወደደ የሚሸቅጠው ተራ ነገር ሆነና ከተጻፈበት ይልቅ ያልተጻፈበትን «እንዲህ እንደሚል» ተብሎ ይሰበክ ጀመረ።

የተጻፈውን ብቻ አሜን ብሎ መቀበልና እሱ እንደሚል ብቻ ለመሔድ መሞከር እንዴት ካለ ልበ ቀና ሰው የሚመጣ ድርጊት ነው? ይህ ነው በዘመናችን የጠፋው እውነት። «በጠበበውና በብቸኛው መንገድ ሂድ» ሲባል «ለምን ተብሎ በጠበበው? ሰፋ ሰፋ ያሉ በርካታ መንገዶችን ማዘጋጀት እየቻልኩኝ» የሚል መልስ ይሰጣል «ይህ መንፈሳዊ ሕይወት ነውና አምልኮህን መንፈስ ለሆነው አምላክ በመንፈስ አድርገው» ስትሉት «አምልኮን ለመፈጸም ኢየሩሳሌም ካልሄድኩ እንዴት ይሆንልኛል?» ሲል ይመልስልዎታል ።«በቀጥታ ብትፀልይ መልስ ሊሰጥህ የሚፈልግ አባት አለህ» ካሉት ነገር መጣ «እነ እን ቶኔስ እነ እከሌንማ ሳልይዝ በፍጹም» ይባላሉ።

ካሉን ለቁጥር የሚያታክቱ መካከለኞች ውስጥ ፊት አውራሪዋ በማርያም ስም የምትታወቀዋ ናት። በቤተክርስቲያናችን አስተምሮ ማርያም «ከፈጣሪ በታች ከፍጡራን በላይ ናት»። ስለዚህ ያለ እርሷ የሚሆን ጉዞ አስቸጋሪ ነው። በዚህም ምክንያት ይመስላል በርካታና በርካታ ድርሰቶች ተደርሰውላታል። ይህች በማርያም ስም የምትጠራዋ በእነዚህ ድርሰቶች ውስጥ «ከፈጣሪ በታች» የሚለውን ብሄል ሰርዛዋለች ወይም አስርዛዋለች። እኛ ተቀብልነውም አልተቀበልነውም አሁን እርሷ ከፈጣሪ እኩል እንደውም በላይ ነች።

በዛሬው እትማችን ይህንን ከተለያዩ የቤተክርስቲያቸናችን ድርሰቶች እናያለን። በቁጥር አንድ እትማችን እንደገለጽነው ዓላማችን ራሳችንን ከእግዚአብሔር ቃል አንጻር ፈትሸን ነቀፋችንን ለማስወገድ ነው እንጂ ልበ ክፉዎች እንደሚሉት «አሁን ያለው ቤተክርስቲያን ፈርሶ ሌላ ይገንባ» ዓይነት ሐሳብ የለንም። እግዚአብሔርም እርሱን ይጸየፈዋልና ከእንደዚህ ዓይነት ድርጊት ፈጽሞ የራቅን ነን። ማርያምንም በተመለከተ እኛ የክርስቶስ እናት ማርያም እንደዚህ ናት እንዳሉልን ልብ ይበሉ። ከመጽሐፍ ቅዱስ ሐሳብ ጋር የምንስማማ ነንና መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እውነተኛዋ ማርያም የሚለውን ሁሉ በደስታ የምንቀበል ክርስቲያኖች ነን። እርስዎስ ስለማርያም ምን ያስባሉ? ጽሑፉን ያንብቡትና የሚለማመትን ይጻፉልን።

ዳግማዊት ማርያም ?

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በማርያም ስም የተጠሩ ከሰባት ያላነሱ ሴቶች መኖራቸውን በቁ. 1 እትማችን መግለፃችን ይታወሳል። በተለያየ ህይወት ውስጥ ያለፉት እነዚህ የክርስቶስ እናት ሞክሼዎች እያሉ ይህ ስም ለእርሷ ብቻ የተገባ እየመሰላቸው «ማርያም ማለት መርህ ለመንግስተ ሰማያት» (ወደ ምንግስተ ሰማያት መርታ የምታስገባ) ማለት ነው የሚሉ ወገኖች ልብ ቢሉት መልካም ነው! (ዘፀ 15:20። 1ኬና. 4:17። ዮሐ. 11: 1፤19 :25) የኢየሱስ እናት ማርያም ናዝሬት በተባለች ሀገር በገሊላ ከተማ ትኖር ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ ማርያም ዮሴፍ ለተባለ ጻድቅ ሰው ታጭታ እንደነበር ይናገራል (ሉቃ. 1:26-27)። የማርያምን ልደት የዘር ሐረግ ይተርካል የተባለው በንጉስ ዘርዓያዕቆብ አስገዳጅነት የቤተክህነት አገልጋዮች በርካታ ድርሰቶችን በጻፉበት ወቅት የተደረሰው ተአምረ ማርያም የተባለው መጽሐፍ የአባቷ ስም ኢያቄም የእናቷ ስም ሐና ሲሆን እናቷ ከካህናት ወገን አባቷ ደግሞ ከነገደ ይሁዳ ነው እያለ ይተርካል። (ተአምረ ማርያም ገፅ 23) መጽሐፍ ቅዱስ ዓላማው ይህ ስላልሆነ የቅድስት ማርያምን የህይወት ታሪክ አልዘረዘረም ስለ ቅድስት ማርያም የሚለው ነገር ቢኖር

- ⇨ ለዮሴፍ የታጨች ነገር ግን በስጋ ሳይደርስባት በድንግልና የነበረች (ማቴ 1: 19-20)።
- ⇨ ከሴቶች መካከል የተባረከች ጸጋን የተሞላች (ሉቃ 1: 28)
- ⇨ ከጌታ የተነገረላት ቃል ይፈፀማልና ያመነች ብጽዕት (ሉቃ1: 45)
- ⇨ የኢየሱስ እናት (ሐዋ1: 14)

በማለት ቅድስት ማርያምን ይገልፃታል ከዚህ ተቃራኒ በሆነው መልኩ የተለያዩ የቤተክርስቲያናችን መጻሕፍት ስለ እርሷ ብዙ ይላሉ። በመሠረቱ የምናነባቸው ሁሉ የኢየሱስ እናት ማርያም ነኝ ያላለቻቸውና ያልሆነቻቸው ናቸው።

- ❖ ማርያም ማለት መንግስተ ሰማያት መርታ የምታስገባ (ተአምረ ማርያም የዘወትር መቅድም ገጽ 9)
- ❖ የእመቤታችን መልክ እንደ አምላክ መልክ ነው: (ገጽ 11)
- ❖ ንጽሕት በመሆኗ አምላክ እንዲያድርባት አደረጋችው (ገጽ 11)
- ❖ ለእናንተ ለኃጥአን መድኃኒታችሁ ናት (ገጽ 11)
- ❖ የመላእክት እህት (ይዌድስዋ መላእክት የጸሎት መጽሐፍ)
- ❖ የኖህ መርከብ (ይዌድስዋ መላእክት የጸሎት መጽሐፍ) የመሳሰሉትን ይላታል።

Scanned by CamScanner

እግዚአብሔር ተስፋ በገባው መሠረት አንድያ ልጁን ከሴት እንዲወለድከደረገ (ገላ. 4:4) ክርስቶስ ከቤተ እስራኤል በስጋ መጣ (ሮሜ 9:5)። ድንግሊቱ የእስራኤል ልጅም ከአእምሮዋ ከዕውቀቷ በላይ በሆነ ነገር ኢየሱስን ወለደች። የጌታ በጎነት ከቤተሰቦቿ ኃይማኖተኝነት የመነጨ መስሏት አንዲት ሴት የተባረከ ቤተሰብ ያስገኘችው ፍሬ ለማለት «የተሸከመችህ ማኅጸንና የጠባኃቸው ጡቶች ብፁዓን ናቸው አለችው።» (ሉቃ 11: 27-28) ቃሏን ባይቃወምም ግን እርሱ ሊመሰርት የመጣው መንፈሳዊ ቤተሰብን እንጂ በስጋ የሆኑትን አልነበረምና ቃሉን የሚሰሙ ብጹአን እንደሆኑ በግልጽ ተናገራት። ምናልባትም በስጋ ቤተሰቦቹ ነን የሚሉት ይህ ስላልገባቸው ይሆናል ክርስቶስ ወደሚያስተምርበት ስፍራ መጥተው ያስጠሩት መንፈሳዊው መምህር «እርሱ ግን ለነገረው መልሶ እናቴ ማን ናት? ወንድሞቼስ እነማን ናቸው? አለው።» (ማቴ 12: 48) ምክንያቱስ ቢባል ለመጣበት ዓላማ ነውና ሙሉ ትኩረቱ በስጋዊ ዝምድና በመጠላለፍ ወደኃላ መዘግየት አልፈለገምና። መጽሐፍ ቅዱስ የቤተሰቹን ዝምድና አልሰወረም። ሌላው ቢቀር ማርያም በመላእክት የምስራች ተብላ የወለደችውን ስምዖን አረጋዊ «የእስራኤል መጽናናት እርሱ ነው» ያላትን ኢየሱስን በኢየሩሳሌም ከነበረው በዓል ወደቤታቸው ከዮሴፍ ጋር ሲመለሱ የ12 ዓመቱ ኢየሱስን በቤተመቅደስ ትታው መጥታ እንደገና ስትፈልገው እንደነበር ይናገራል (ሉቃ. 2:41) ።

ማርያም ከክርስቶስ ደቀመዛሙርት ጋር አብራ በኢየሩሳሌም በፀሎት ትበረታ ነበር። መንፈስ ቅዱስም በወረደ ጊዜ አብራቸው ነበረች (ሐዋ. 1:14)። መጽሐፍ ቅዱሳችን ስለ ማርያም እንዲህ ባለ ሁኔታ ነው የሚያስተምረን የመድኃኒዓለም አማኞች እግዚአብሔር በእርሷ ካደረገው ነገር የተነሳ« ትውልድ ሁሉ ብጽዕት ይሉኛል።» እንዳለችው በፅዕት ይሏታል። በእርግጥ ማርያም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካሉና የመልካም ምሳሌ እንደነበራቸው ሴቶች ሁሉ እርሷም ግሩም አብነት (አርአያ) የነበራት ሴት ነች። በቤተመቅደስ አገልግሎት ዘመኑን ከጨረሰው ከዘካርያስ ይልቅ የተሻለ እምነት የነበራትና «እነሆኝ የጌታ ባሪያ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ» (ሉቃ 1:38) ያለች ሴት ናት እኛም አምላክ ያለው ይሁን ማለትን ከማርያም ልንማር ይገባናል። ግልፅ ከሆነው የእግዚአብሔር ቃል በመውጣት መናፍቃን ብዙ የራሳቸውን ነገር ተናግረዋል ፅፈዋል። ዛሬ በቤተክርስቲያናችን ክስመ ስላሴ ባልተናነሰ (አንዳውም በይበልጥ !) ከክርስቶስ አዳኝነት በላቀ (በተሻለ) ሁኔታ ስለማርያም ብዙ ይባላል።

ይህን ያስተዋሉ አንድ መምህር «ማርያምን መንፈቅስ እግዚአብሔር እያደረች ያለች አስመሰሏት» በማለት ትዝብታቸውን አኑረዋል። ማርያምን በእግዚአብሔር መንበር ላይ ያስቀመጧትን ከክርስቶስ የማዳን ስራ ይልቅ የተሻለች አድርገው ያኖሯትን የተረገሙ ጽሑፎች (ስብከቶች) ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር እያነጻጸርን ልናይ ወደናል።

❖ «ስለእናትሽ ስለ ሐና ብለሽ ስለአባትሽ ስለኢያቄም ብለሽ ድንግል ማኅበራችንን ዛሬ ባርኪልን» (መዝገበ ፀሎት የዘወትር ፀሎት)

እዚህ ላይ የምናያት ማርያም አማላጅ ወይም እኛ እርሷን ጠይቀን እርሷ ሌላ አካል (እግዚአብሔርን) ለምና የምንፈልገውን የምታስገኝልን ሳትሆን ራሷ በገዛ ስልጣኗ ሁሉን የምታደርግ ተለማኝ (ተማላጅ) የሆነችዋን ማርምን ነው በመጽሐፍ ቅዱሳችን ላይ «ስለ አባታችን ስለ አብርሃም ስለ ባርያህ ስለ ይስሐቅ ስለ መረጥኸውም ስለ እስራኤል ብለህ ኪዳንህን አስብ» ተብሎ የተጻፈውን በመገልበጥ ለማርያም የተደረገ ይመስላል።

❖ «የእግዚአብሔር መላእክት ሲወጡባት ሲወርዱባት ያዕቆብ ያያት መሰላል አንቺ ነሽ።» (ማክሰኞ ውዳሴ ማርያም)

አማላጅ ነች ለማለት የቀረበ የኑፋቄ ትምህርት ነው። ጸሐፊዎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ዕውቀታቸው ደህና ይመስላል። ግን ይህን ዕውቀታቸውን የተጠቀሙበት መንገድ በጣም ትልቁ የጥፋት ጎዳና መሆኑ ያሳዝናል። መድኃኒታችን «እውነት እውነት እላችኋለሁ ሰማይ ሲከፈት የእግዚአብሔርም መላእክት በሰው ልጅ ላይ ሲወጡና ሲወርዱ ታያላችሁ» ያለውን የውዳሴ ማርያም አዘጋጅ ነው የሚባለው አባ ሀርያቆስ «የለም ይህ ለማርያም እንጂ ለአንተ አይደለም» በሚል ግልጽ ማወናበድ ለማድረግ ሞክሯል (ዮሐ. 1:52)

❖ «ማርያም ሆይ መላእክት ያገኙሻል ሱራፌልም ያመሰግኑሻል። » (አርብ ውዳሴ ማርያም)

ክብር ለሚገባው ክብርን መስጠትና የማይገባውን ነገር ማድረግ የተለያዩ ነገሮች ናቸው። በዚህ ክፍል የምናየው ለማርያም የሚገባትን ክብር መስጠትና «እግዚአብሔር የመረጣት በፅዕት ናት» ከማለት የዘለለ ለአምላክ ብቻ የሚገባውን ውዳሴ ለፍጡር የተሰጠበትን ድፍረት ነው። መጽሐፋችን ላይ መላእክት ለልዑሉ «አንዱም ለአንዱ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ምድር ሁሉ ከክብሩ ተሞልታለች» እያሉ ሲያመሰግኑት ያየው ጸሐፊ ለማርያም ሳይሆን በማርያም ስም ለሚያምናት እመቤቱ ይህን ጥቅስ ለእርሷ ለማድረግ ወደደ (ኢሳ 6:3) ይህ ግን ትልቅ የምንፍቅና ጎዳና ነው!

Scanned by CamScanner

❖ «የዘላለም ሕይወት ድልድይ ትሆኚ ዘንድ የዓለም ሁሉ መድኃኒት ሆይ ለምዕመናን ወገኖችሽ መድኃኒታቸው ልትባይ ይገባሻል።» (አንቀጸ ብርሃን ገጽ 50 ቁ 12)

ሀላችን በኃጢአት ደዌ ተይዘን በነበርንበት ወቅት መድኃኒት የሆነን መድህን ዓለም ክርስቶስ እንደሆነ ራሱን ክርስቲያን ነኝ ብሎ የሚጠራ ሁሉ የሚለማማበት እውነት ነው። መልአኩ ለዮሴፍ ታይቶት ባነጋገረው ወቅት «ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ» ነው እንጂ የማርያምን መድሐኒትነት አላበሰረውም (ማቴ 1:21)።

የዘላለም ሕይወትንም በተመለከተ የእግዚአብሔር ዓላማ እንዲህ ነው «በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።» (ዮሐ.3:16) ምንም ማሻሻያ የማይደረግበት የእግዚአብሔር መሻት ሀላችን በልጁ በኩል እንድናገኘው ነው።

የአንቀጸ ብርሃን አዘጋጅ ይህ ቅር ያሰኘው ይመስላል። ለዚህም ነው «መንፈሴም በአምላኬ በመድኃኒቴ ሐሴት ታደርጋለች» (ሉቃ.1:47) ያለችውን የማርያምን ቃል ቸል በማለት የለም አንቺ ራስሽ መድኃኒት ነሽ እንጂ እንዴት መድኃኒትያስፈልግሻል በማለት የጻፈው ። አምላካችን ግን እንዲህ ብሎናል። «እኔ እኔ እግዚአብሔር ነኝ ከእኔም ሌላ የሚያድን የለም ተናግሬአለሁ አድኜማለሁ አሳይቼማለሁ» (ኢሳ. 43:11-12) እኛም አሜን ብለናል።

✞ «በማንና በምንስ ምሳሌ እንመስልሻለን » (ቅዳሴ ማርያም ገፅ 29)

ምን ያህል በድፍረት እንደተኬደ እግዚአብሔርንስ በምን ያህል እየተፈታተነው እንደሆነ ይህ ክፍል ማሳያ ሊሆነን ይችላል። በምህረቱ ባይጎበኘን ኖሮ እንደሰዶምና ገሞራ በጠፋንና ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር ነበረች በተባለልን ነበር ምክንያቱስ ቢባል «እንግዲህ እግዚአብሔርን በማን ትመስሉታላችሁ? ወይስ በምንስ ምሳሌ ታስተያዩታላችሁ» የሚሰውን ምንባብ በቀጥታ በመውሰድ ለፍጡር (ሊያይውም እርሷ ነኝ ይሰማማኛል ባላለችው) መስጠቱ ከቅጣት በላይ አይገባንም ትላላችሁ? ከዚህስ የተሻለ ምን እንጠብቅ ይሆን ? (ኢሳ.40:18)

✞ «ድንግል እመቤቴ ሆይ ነፍሳትን ሁሉ የምትመግቢ ነሽና የልብስና የምግብ ችግር ባለ ዘመኔ ሁሉ አታሳይኝ» (መልክአ ኤዶም ቁ.5)

እንደቸርነቱ ለፍጥረታት ሁሉ የሚቀምሱትን የሚሰጥ ዓለማትን ለዘመንና ለዘመናት ሲመግብ የኖረ የፍጥረት ሁሉ ጌታ ሁሉን ቻይ አምላክ ስላለን በጣም

እድለኞች ነን። ፍጡር ቢሆን ይህን ስራ የሚሰራው እርሱ መኖር ከመጀመሩ በፊት የነበሩ ሰዎች ባለቁ ነበር እርሱም ባልተገኘ ነበር። ከእርሱም መሞት በኋላ ምድር ወና በሆነች እንዳችም ባልተገኘባት ነበር አባታችን እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁንና እንዲህ እንዲሆን አልፈቀደም። ከላይ ያነበብነውን ጸሎት ታዲያ እንዴት እንየው ? ቢባል አስቸጋሪ ነው። የጸሐፊው ማርያምን እኛ አናውቃትም። የክርስቶስ እናት ማርያም ግን መጀመሪያ ያላት እንደ ፍጥረታት ሁሉ ሞትን የቀመሰች ናትና «ነፍሳትን ሁሉ የምትመግቢ» ለመባል አይቻላትም። ቀደም ሲል እንዳልነው እርሷ ከመወለዷ በፊት እልፍ አእላፍ ነፍሳትን ለመመገብ የእርሷ አስተዋፅኦ አልነበረምና። ሊያውስ ከተወለደች በኋላ የእርሷን ምግብ ሁኔታ ሰዎች ምን ይሻላል እያሉ ሲጨነቁላት መልአክ የምትበላው ይዞላት መጣ እየተባልን አይደል የምንሰበከው? ታዲያ እንዴት እርሷ ለነፍሳት ሁሉ ምግባቸውን መስጠት ይቻላታል ?

አንድ ነገር በድፍረት የምንናገረው እርሷ በእንደዚህ ዓይነት የክህደት ትምህርት ውስጥ የለችበትም። እርሷስ ያለችው «የተራቡትን በበጎ ነገር አጥግቦአል» (ሉቃ. 1:53) ብቻ ነው እንጂ የእኔ እገዛ ከሌለበት ምድር አበቃለት አይደለም። «እንግዲህ ምን እንበላለን? ምንስ እንጠጣለን? ምንስ እንለብሳለን ? ብላችሁ አትጨነቁ ይህንስ ሁሉ አህዛብ ያፈልጋሉ ይህ ሁሉ እንዲያስፈልጋችሁ የሰማዩ አባታችሁ ያውቃልና።» (ማቴ. 6:31-32)

✞ «ለዕውራን ብርሃናቸው ለተጠሙትም የወይን ምንጫቸው» (መልክአ ኤዶም ቁ.11)

ዕውራን እንዲያዩ ማድረግ መቻል ከእግዚአብሔር የሚገኝ ፀጋ ነውና ይህን ያገኘ ሰው ክብሩን ለራሱ ሳሆን ለእግዚአብሔር መተው ይኖርበታል። አለበለዚያ ያንንም ፀጋ ያጣና ከእግዚአብሔር የራቀ ሰው ይሆናል። ማርያም ለዕውራን እንዲያዩ ብርሐን መስጠት አይደለም እንደ አዲስ ዓይን መፍጠር ብትችል የሚቃወም ሰው የሚኖር አይመስለንም። አሁን ግን እርሷ ያለችው ሁላችን እንደምናውቀው መልካሙን ነገር በእርሷ ያደረገውን አባታችንን ቀንና ማታ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እያሉ ከሚያመሰግኑ ለቁጥር ከሚከብዱ ቅዱሳን ጋር አብራ በማመስገን ላይ ነች። አበቃ! አሁን ብርሐን መፍጠር ለተጠሙ ማርካት

Scanned by CamScanner

አይቻላትም። ይህን ማድረግ የሚችለው አንድ ብቻ እርሱም «ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ » (ዮሐ. 7:37) ለማለት የተገባው ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው።

ስለ ብርሃንም ቢሆን ማየት ለተሳናቸው (በስጋ) ብቻም አይደለም ሕይወቱ ለጨለመበትም ጭምር «እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ የሚከተለኝም እርሱ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም።» ለማለት የቻለው አንድ እርሱ ክርስቶስ ነው ክብር ለስሙ ይሁን አሜን (ዮሐ. 8:12)

ብንዕፍ አንጨርሳቸውምና እዚህ ላይ እናቁም። አንድ ነገር ግን ልብ እንበል ቅድስት ማርያም ቀደም ሲል እንዳልነው በዚህ ዓይነቱ ወንጀል ውስጥ የለችበትም። እርሷ ራሷን ዝቅ አድርጋ «የባሪያይቱን ውርደት ተመልክቷልና» (ሉቃ. 1: 47) ነው ያለችው። ይህ ለትህትና ተብሎ የተነገረ ቃል የሚመስላቸው ቢኖሩ ግና የእግዚአብሔር ልዕልና የእኛ የፍጥረታቱ ምናምንቴነት አልገባቸውምና ነው። በፊቱ ስንታይ የአዋራ ብናኝ ያህል ከምንሆን ከእኛ መካከል መመረጧን እንደ ልዩ መታደል ልትቆጥረው ብቻ አይደለም እኛም ልንገረምበት ይገባል። ግና መመረጧ ከእርሷ እንዳልሆነ ይልቁንስ ከመራጩ ቸርነት እንደሆነ ገብቷታልና ነው እንዲህ ማለቷ። ታዲያ ወገኔ መመስገን የሚገባው መራጩ ወይስ ተመራጩ ? ሁለቱም እንደማትለኝ ተስፋ አደርጋለሁ ካልከኝ ግን ተመራጩ ምን አድርጎ? በምን ስራው? ብዬ እጠይቅሃለሁ ።እንዲህ ዓይነቱን አስተምሮ ይዘው የተነሱ ራሳቸውን «ማህበረ ቅዱሳን» ብለው የሰየሙ ክፍሎች ማርያም ፅዮን ናት የሚለውን ትምህርት ይዘው መንቀሳቀስ ከጀመሩ ሰነባበቱ።

«አንዳንድ ሰዎች ለከተማይቱ ለሕዝቦቿም የተነገረውን ለእመቤታችን ከተነገረው ሳይለዩ እያምታቱና እያደባለቁ እመቤታችን አይደለችም ለማለት ይሞክራሉ። . . . ለምሳሌ ያህል <ሰው እናታችን ጽዮን ይላል በውስጧም ሰው ተወለደ> የሚለውን አነጋገር ለከተማ እንጂ ለሰው አይደለም፤ ስለዚህ እመቤታችን አይደለችም ሊል አይችልም። እነዚህ ሰዎች <ብውስጧም ሰው ተወለደ> በሚለው ዘይቤ ምክንያት ጽዮን ሀገር ናት ካሉ ለዚያውም በኢየሩሳሌም ያለችውን አንዲት

ቦታ አውሮፓውያንም አሜሪካውያንም አፍሪካውንም ሌላውም እንዴት እናታችን ሊላት ይችላል?... » (ሰምዐ ጽድቅ ጥር 1996 ዓ.ም 11ኛ ዓመት ቁጥር 9. ገፅ 8)

ማህበረ ቅዱሳኖች ይህንን ያሉት መዝ. 86:5-6ን ተተንተርሰው ነውና እርሱን እያየን ለምን አንነጋገርም? «ሰው እናታችን ጽዮን ይላል በውስጧም ሰው ተወለደ እርሱ ራሱም ልዑል መሠረታት እግዚአብሔር ለህዝቡ በውስጧም ለተወለዱት አለቆችዋ ይነግራቸዋል» ይህንን ብቻ (ከፍና ዝቅ ሳንል) ስናየው ለማርያም የማይሰማሙ ነገሮችን እናገኛለን ማህበረ ቅዱሳኖች ነገራቸውን በጥያቄ ነውና ያስቀመጡት እኛም መልሳችንን በጥያቄ እያደረግን እንዲመልሱልን ብንጠይቅስ፡-

- ምንባቡ «በውስጧም ሰው ተወለደ» ነውና የሚለው በሰው ውስጥ ሰው እንዴት ይወለዳል? ይህ የገባቸው አንድ ጸሐፊ <u>በውስጧ</u> የሚለውን <u>ከእርሷ</u> በሚለው ተክተውታል (እናታችን ጽዮን ገጽ. 31-32)
- «ልዑል መሠረታት» የሚለውን በሰውኛ ምን የሚል አንድምታ ልነሰጠው ይቻለናል?
- በውስጥዋ የተወለደው አንድ ብቻ ሳይሆን በርካቶች ናቸውና ማርያም ከኢየሱስ ሌላ ልጅ የላትም ከሚለው ትምህርታችን ጋር አይጋጭም? ለዚያውም በውስጥዋ የተወለዱት ልጆቿ መልሰው አለቃ ይሆኑባታል። ይህንስ ከማርያም ጋር እንዴት እናጣጥመው ይሆን?

ማህበረ ቅዱሳኖች አውሮፓውያንን አሜሪካውያንና አፍሪካውያንንም ጠቅሰዋል። «እናታችን» የሚላት የዓለም ማህበረሰብ እንደሆነ ለማሳየት የተጠቀሙበት መንገድ ነው። ለዚህም ሰበብ የሆናቸው ቁ.4 ላይ «የሚያውቁኝን ረሃብንና ባቢሎንን አስባቸዋለሁና እነሆ ፍልስጥኤማውያን ጢሮስም የኢትዮጵያም ሕዝብ እነዚህ በዚያ ተወለዱ» የሚለው ነው። ይህን ሲያዩ «እናታችን» የሚሏት ፍጥረታት በመላው መሰላቸው። ግን ቁ. 4ን ጨርሰው ቢያነቡት ኖሮ «እነዚህ በዚያ ተወለዱ» የሚለውን ያገኙት ነበር (ምናልባትም አንብበውት እንዳላዩት ቸል ካላሉት) እነዚህ ወገኖች የተዘረዘሩት የትውልድ ሀገራቸው የተለየ መሆኑን በፅዮን የሚወለዱትም የተለየ የትውልድ ስፍራ እንደሌቸው ለመግለጽ ነው። የቃሉን መልዕክት ከተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች እንየው፡-

Scanned by CamScanner

- «በእርግጥም ስለ ፅዮን ይህም ያም ሰው በእርሷ ውስጥ ተወለዱ፤ ልዑልም ራሱ ያጸናታል ይባላል። እግዚአብሔር ሕዝቡን ሲመዘግብ ይህ ሰው የተወለደው በዚያ ነው ብሎ ይጽፋል።» (አዲሱ መደበኛ ትርጉም 1993 ዓ.ም.)
- «በፅዮንም ልዩ ልዩ ሰዎች ተወለዱባት ይላሉ። እርሱም ልዑል ያጸናታል እግዚአብሔርም አሕዛብን በጽፈት ቁጥር ይህና ይህም ከዚያ ይወለዳሉ ይላሉ።» (በ1879 ዓ.ም. የታተመው መጽሐፍ ቅዱስ)
- «መንግስታት ሁሉ በኢየሩሳሌም ስለተወለዱ ሁሉም ፅዮንን እናታችን ብለው ይጠሩአታል፤ ልዑል አምላክም ታላቅ ያደርጋታል። እግዚአብሔር ህዝቦችን ሁሉ ይመዘግባል እያንዳንዱንም በጽዮን የተወለደ ብሎ ይጠራዋል።» (ቀለል ባለ አማርኛ የተተረጎመ 1980 ዓ.ም)«ዘማዊቷ ጽዮን ወይስ ድንግሊቱ ማርያም?» ከተሰኘው ያልታተመ መጽሐፍ የተቀነጨበ)

የማርያም ምልጃ

«ምልጃ አማለደ መሠረታዊ ትርጉሙ አንዱ ስለ ሌላው መለመን» ማለት እንደሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ይነግረናል (ገጽ 56) በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ስንመለከት በርካታ ሠዎች (ካህናት ነበያት፣ ነገስታት) እንዲሁም መላእክት በእግዚአብሔርና በህዝቡ መካከል በመግባት የምልጃ ሥራ ሠርተዋል። ግን ይህ የምልጃ ሥርዓት ሁኔታዎች ገድበውት ታይቷል። በዚህ ምክንያት በየጊዜው የተሰያዩ አዳዲስ መካከለኞች (አማላጆች) ሲታዩ ቆይቷል። በቤተክርስቲያናችን አስተምዕሮ ማርያም በምልጃ ሥርዓት ውስጥ ቀዳሚውን ስፍራ ይዛ ትገኛለች ለዚህም እንዲረዳ «መትሐተ ፈጣሪ መልዕልተ ፍጡራን» ማለትም« ከፈጣሪ በታች ከፍጡራን በላይ» የሚል ስያሜ ሰጥተናታል።

ስለማርያም አማላጅነት በቤተክርስቲያናችን ሰዎች የተጻፉትን መጻሕፍት ከማየታችን በፊት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለማርያም አማላጅነት ይሰማማሉ የሚባሉትን ጥቅሶች እንይ፦

1) ዮሐ. 2:1-11 «በሦስተኛው ቀን በገሊላ ቃና ሰርግ ነበር የኢየሱስም እናት በዚያ ነበረች ኢየሱስም ደግሞ ደቀ መዛሙርቱን ወደ ሰርጉ ታዳሙ።» እነዚህ ሰዎች (የሰርግ ደጋሾቹ) ምናልባት ከማርም ጋር ዝምድና ይኖራቸዋል፤ ማርያም ተጋባዥና ተስተናጋጅ ብቻ አትመስልም። ምክንያቱም የወይን ጠጁን ማለቅ ከሰዎች ሰምታ ሳይሆን በጓዳው ስራ (በመስተንግዶው) እየረዳች ስለነበረች ያወቀች ይመስላል። እዚህ ጋር የምልጃን አንዱን ገጽታ እናጣዋለን ። ማንም ሰው ለማርያም «ለልጅሽ ነግረሽ ከጉድ አውጭን» አላላትም ሌላኛው ደግሞ የማርያም አነጋገር ነው «የወይን ጠጅ እኮ የላቸውም» የሚለው የእርሷም በነገሩ መጨነቅና ምን ይሻላል? የማለት መንፈስ ያለው ንግግር እንጂ እባክህ ልጄ ወዳጄ የሚል አይደለም። ቀደም ሲል በብሉይ ኪዳን ብዙ ሰዎች ለሰዎች በምልጃ ቆመው ለውጥን እንዳመጡ ተነጋግረን ነበር። ይህም ነገር በአዲስ ኪዳን በብዙ ገፅታ ታይቷል ።

- መቶ አለቃው ጠይቆ ልጁን ከሽባነት ታድጓል (ማቴ. 8፡ 5 - 8)
- መኮንኑ እንዲሁ ጠይቆ የሞተች ልጁን ትንሳኤ አይቷል (ማቴ. 9:18-26)
- ከነናዊቷ ሴት ልጇን ከጋኔን አስራት ነጻ እንዲወጣ ጠይቃ ተሳክቶላታል (ማቴ 15:21)
- የአይሁድ ሽማግሌዎች ለመቶ አለቃው ለምነው የመቶ አለቃው ባሪያ ሊሞት ከነበረበት ሁኔታ ታድገውታል (ሉቃ.7:1) እነዚህ ክፍሎች እንደሚያሳዩት ከማርያም የማማለድ ስራ ጋር (የማርያምን ጥያቄ እንደማማለድ ብንቀበለው እንኳን) በተመሳሳይ ሁኔታ ነውና ጥያቄአቸውን ያቀረቡት እነዚህንም ወገኖች «አማላጆቻችን» የማናደርግበት ምክንያት ምን ይሆን ?

Scanned by CamScanner

2) ማቴ 10፡ 40-42 «እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበላል እኔንም የሚቀበል የላከኝን ይቀበላል ነብይን በነብይ ስም የሚቀበል የነብዩን ዋጋ ይወስዳል። ጻድቅንም በጻድቅ ስም የሚቀበል የጻድቁን ዋጋ ይወስዳል። ማንም ከእነዚህ ከታናናሾቹ ለአንዱ ቀዝቃዛ ጽዋ ውኃ ብቻ በደቀመዝሙር ስም የሚያጠጣ እውነት እላችኋለሁ ዋጋው አይጠፋበትም።» ይህ ክፍል በፍፁም ለማርያም የማይሆን ክፍል ነው። ለነገሩማ መምህራኖቻችን ለማርያምም ብቻ ሳይሆን ለመላእክትም እንደሚስማማ ነው የሚነግሩን ግን ማርያምም ሆነ መላእክት ነብይ ወይም ጻድቅ እንዲሁም ደቀመዝሙር እንዳልሆኑ ይታወቃል።

ምንባቡን ከቁ. 1 ጀምሮ ስናየው ደቀ መዛሙርቱን ወደ አገልግሎት እየላከ ስላለው ሁኔታ ነው የሚነግረን ምንም ዓይነት «መርቅ ወይም ብር ወይም ናስ ወይም ከረጢት ወይም ሁለት እጀ ጠባብ ወይም ጫማ ወይም በትር» እንዳይዙ አስጠነቀቃቸው (ቁ. 9-10) «ለሰራተኛ ምግቡ ይገባዋልና» (ቁ.11) የሚገለገለው ሰው ወይም መልዕክቱን ይዘውለት ሲሄዱ መልእክቱን በደስታ የሚቀበለው ሰው እርሱ ይዘውት ስለመጡት መልእክት የሚገባቸውን ሊሰጣቸው ይገባል።

በደቀመዝሙር ስም የምንቀበለው ማንን እንደሆነ ክርስቶስ እዚያው ላይ «ከእነዚህ» በማለት ለይቶ ፊት ለፊቱ በወቅቱ የነበሩትን እንደሆነና ከዚያም አንጻር አሁን የእግዚአብሔርን ቃል ሊነግሩን የሚመጡትን ወገኖች መሆኑን ምንም ተጨማሪ ትርጉም በማያስፈልገው ቃል ነግሮናል።

እንግዲህ ከዚህ ተነስተን ስናየው ከማርያም ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት እንደሌለው ግልፅ ነው። ብዙዎች ይህን ክፍል የሚሰብኩት «ለደቀ መዝሙር ስም ለችግረኞች ውሃ ብናጠጣ (ገክር ብናዘክር) ዋጋችን አይጠፋም» በሚል መንፈስ ነው ጌታ ይህን የተናገረው ለቅዱሳኑ ቃል ገብቶ ነው እያሉ የዋሃን መበለቶችንም ያስቱበታል። እነዚህ ወገኖች ይህን «ስብከት» እያደመጡ ከእለት ጉርሳቸው እየነጠቁ ግማሾቹም እየለመኑ ይደግሳሉ፤ እነ ሆድ አምላኩም ከልደታ - ማርቆስ (1-30) ባሉት ቀናት የመበለቶችን ቤት ያራቁታሉ።

የማቴዎስን መልዕክት በአጭር ግን ግልጽ ቃል ማርቆስ ወንጌል ላይ እንዲህ እናገኘዋለን። «የክርስቶስ ስለሆናችሁ በስሜ ጽዋ ውኃ የሚያጠጣችሁ ሁሉ ዋጋው እንዳይጠፋበት እውነት እላችኋለሁ።» (ማር. 9፡ 41) አሁን ደግሞ ለቁጥርም ለሆነ ለቆጣሪ ወደሚያስቸግሩት ወደ ቤተክርቲያን መጽሀፍቶቻችን እንመለስ።

- «በልቤ ያለውን ምኑን ስንቱን አነግርሻለሁ ኃዘኔን ጭንቀቴንም ስንቱን አነግርሻለሁ? ኀዘኔን ጭንቀቴንም ሁሉ አንቺ ታውቂዋለሽና» (መልክአ ኤደም ቁ.3).

አሁን ደግሞ ሁሉን አዋቂዋን ማርያምን ነው የምናገኘው ከሰውነት ባህሪ ወጣ ያለችና ምንም ከእርሷ የሚሰወር የሌለ እንደሆነች ነው የተገለጸው። መጽሐፍ ስለ እርሷ የዘገበላት ማርያም ግን ከሰውነት የዘለለ ምንም ዓይነት ባህሪ የላትምና ሄሮድስ ልጇን ሊገለው መፈለጉን እንኳን መልአኩ ለዮሴፍ እስኪነግረው ድረስ አላወቀችም። ይህም ብቻ አይደለም አንድዬ ልጇ ቤተ መቅደስ ውስጥ ቀርቶ ጠፍቶባት በነበረ ጊዜ የት እንደሆነ ማወቅ ስላልቻለች ብዙ ለመፈለግ ተግዳ ነበር በኋላ ስታገኘው «እናቱም ልጅ ሆይ ለምን እንዲህ አደረግህብን? እነሆ አባትህና እኔ እየተጨነቅን ስንፈልግህ ነበርን አለችው።» እንግዲህ እኛ የምናውቀው አጠገቧ ያለውን የምታየውን ብቻ የም ታውቀውን የኢየሱስ እናትን ብፅዕት ማርያምን ነው ቀደም ሲል እንዳልነው የመልክአ ኤደምን ማርያም አናውቃትም።

- «አንቺን መጠጊያ ስላደረግሁ በአንቺ ከመታመን በቀር ሥራዬ ኃጢአት ብቻ ሆኗልና ለእርዳታ ፈጥነሽ ድረሽልኝ» (መልክአ ኤደም ቁ. 3)

«በልዑል መጠጊያ የሚኖር ሁሉን በሚችል አምላክ ጥላ ውስጥ ያድራል።» (መዝ. 90፡1)

የቱን እንቀበልና የትኛውን እንጣል? ነው ወይስ አንድ ከፈጣሪ አንድ ከፍጡር መጠጊያ እናድርግ? ይህ እንዳይሆን ቅዱስ መጽሐፋችን «በፍጡር የሚታመን የተረገመ ነው»ይለናል። ማርያም ፍጡር ለመሆኗ የሚጠራጠር ይኖራል ብለን አናስብም ስለዚህ በርሷ የማንታመነው የተረገመ ላለመሆን ነው። እኛስ የቀድሞ አባቶቻችን «አቤቱ ኃይሌ

Scanned by CamScanner

አምባዬ በመከራም ቀን መጠጊያዬ ሆይ» ብለው እንዳሉት እንላለን (ኤር. 16:19)

- «በምሄድበትም ጎዳና በማድርበትም ቦታ ሁሉ በመልትም በሌሊትም ጥበቃሽ አይለየኝ» (መልክአ ኤዶም ቁ 5)

ቀደም ሲል ሁሉን አዋቂ አደረጋት በመቀጠል መጠጊያና መታመኛ እንደሆነች ለማስመሰል አሰፈረ አሁን ደግሞ ያለማቋረጥ ለፍጥረት ጥበቃ የምታደርግ እንደሆነች ሊነግረን እየሞከረ ነው። ፍጥረታትን ብቻ ሳይሆን አለማትን በመጠበቅ ለዘመናት ሳይደክመው የቆየ ብቻውን (ያለረዳት) ለእኛ መልካምን የሚያስብ የዓለማት ጌታ ሁሉን ቻይ እግዚአብሔር ነው። እንደ እግዚአብሔር ያለ ማንም የለም። ምክንያቱም ሁሉም መጀመሪያና መጨረሻ አለው። ሁሉም ድካም ይነካዋል። ሁሉም የአቅም ማነስ ይፈትነዋል። ሁሉም ሁሉን ማወቅ አይችልም። ሌላም ሌላም እግዚአብሔር ብቻ እነዚህን ሁሉ አሸንፏል። ስለዚህ ነው «እስራኤልን የሚጠብቅ አይተኛም አያንቀላፋም» የተባለው (መዝሙር 120: 4) እኛስ ድካም በማይነካው መሰልቸት በሌለበት በእግዚአብሔር ጥላና ጥበቃ ስር መሆንን ብቻ እንፈልጋለን። እርሱ ለፍጥረቱ የሚራራ ነውና።

ውድ አንባቢ ነገሩን በሃይማኖተኝነትና በስሜት አትመልከተው። ይህ አይነቱ አስተምህሮ ስለ ሁላችን ዋጋ የከፈለልንን የክርስቶስን ሞት ከንቱ የሚያደርግ መሆኑን አስተውል። ይህን በመስበክና ህዝቡን ወደ ጥፋት የሚወስዱት ሁሉ በህያው እግዚአብሔር እጅ መውደቃቸው የሚቀር ይመስልሃል? ቅዱስ መጽሐፋችን «ጠላቶች ሳለን ከእግዚአብሔር ጋር በልጁ ሞት ከታረቅን ይልቁንም ከታረቅን በኋላ በሕይወቱ እንድናለን» እያለ ሲናገር የተመለከተው መናፍቅ «ስለ አንቺም ከምድር ወደ አርያም ወደ መንግስተሰማያት የቀረብን ሆንን» (አንቀጸ ብርሃን ገጽ 50) ማለቱን «የተረገመ ወንጌል» (ገላ. 1: 7) ማለታችን ማርያምን መንቀፋችን ተደርጎ ይቆጠራልን? መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ምልጃ የሚለውን እውነት አብረን እንመልከት።

በኃጢአታችን ምክንያት በጻድቁ አምላካችንና በበደለኞቹ በእኛ መካከል የኃጢአት ግድግዳ ተሰርቶ ከጸጋው ዙፋን ተለይተን በፍጥረታችንም እንደ ቁጣ

ልጆች እንኖር ነበርን ከሰው ልጆችም መካከል ወደ ልዑል የሚማልድ እንደሌለ ልዑል ስለተረዳ ተደነቀ ስለዚህም የገዛ ክንዱን ወደ ምድር ላከው (ኢሳ. 59:16) በፍቃደ አብ ሰው ሆኖ የተገለጠው የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ በስጋው ሞት በኩል የኃጢአታችንን መጋረጃ በደሙ ቀደደው። እስራኤላውያን ወደ ኢያሪኮ እንዳይገቡ ያገዳቸው የኢያሪኮ ግንብ እንደተደረመሰ (ኢያሱ 7: 20) ወደ አብ ዙፋን እንዳንገባ ያገደንን የኃጢአት ግድግዳ የይሁዳ አንበሳ ኢየሱስ አፈረሰው (ኤፌ 2: 14) ጌታም በመስቀሉ ደም ጥልን ገደለልን ከአብም ጋር ዳግም ላንጣላ ታረቅን ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር «በስጋው ሰውነት በሞቱ በኩል አስታረቃችሁ» ይላል (ቆላ. 1: 22) የሐዲስ ኪዳኑ መካከለኛ (አስታራቂ) ስለኃጢአታችን ራሱን በማቅረቡ ምክንያት ከአብ ዘንድ ስለ እኛ ብቃት አለው ውድ አንባቢ አንተን በእግዚአብሔር ዘንድ ሊወክልህ የሚችለው ስለ አንተ የሞተውና ስለኃጢአትህ አንዳች መስዋእት ያለው አካል ብቻ ነው። እርሱም ክርስቶስ ነው። ሐዋርያው

«አንድ እግዚአብሔር አለና በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው።» (1ጢሞ 2:5) ይላል። መካከለኛው አንድ እንጂ እንደተለማመድነው ለቁጥር የሚያታክቱ አይደለም በርካታዎቹን መካከለኞች ለማየት ከፈለጉ እጅግ ከበዙት መካከለኞቹ መካከል ጥቂቶቹን ብቻ እናሳይዎት።

«በመጽሐፈ ሰዓታት የተክለሃይማኖት ጸሎት ዓለምን አድኗል ተብሏል (የተክለሃይማኖት ስብሐተ ፍቁር ገጽ 215) ገድለ ተክለሃይማኖት በገዘክር ትድናለህ ይላል። (ምዕ2:4-5፤ 9-11) ሌላው ይቅርና ሰይጣንን እንኳን ማጽደቅ ይቻላል ይላል ገድለ ተክለ ሐይማኖት (ም. 48: 1-4) በተለይማ እሁድ እና ሐሙስ እባብ ከገደልክ ጥያቄ የለውም ወደ ጽድቅ መንገድ ገብተሃል (ገድለ ተክለሃይማኖት ም. 51: 6) ተክለሃይማኖት በተቀበረበትም ሆነ ቤተክርስቲያኑ በታነጸበት የተቀበረ ይጸድቃል። (ገድለ ተክለይማኖት ምዕ. 54:12)ገዳሙ ውስጥ ሆነህማ በተቅማጥ ከሞትክ ልዩ ነው የጽድቅ አክሊልን ትቀዳጃለህ(ገድለ ተክለሃይማኖት ም.54:23) የቱን አንስተን የቱን እንተዋለን በርካታ ገዳማት አሉ ሁሉም የተሳለማቸውን ሰው ያፀድቃሉ። እጅግ በርካታ ተአምራት ገድላት ድርሳናት . . . አሉ ሁሉንም ያነበቡ ይጸድቃሉ።

Scanned by CamScanner

ብዙና ብዙ ቅዱሳን ሰዎችና መላእክት አሉ መታሰቢያቸውን ያደረጉ ስማቸውን የጠሩ ሁሉ ይጸድቃሉ። . . . በተመቸዎት ጎዳና ይጓዙ ይጸድቃሉ ተብለው ይሰበካሉ።» (ከቴቄል 1ኛ ዓመት ቁ6. የተወሰደ) ክርስቶስ ግን «በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም» ያለው ለዚህ ነው (ዮሐ 14:6) ቀደን የማናወጣው ወይም የማንሰርዘው የእግዚአብሔር ቃል እኛን በጌታ ፊት ሊወክለን የሚችል ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደሆነ ይናገራል። በ1879 ዓ.ም የታተመው የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ በጥንቱ ቋንቋ ስለ ክርስቶስ ምልጃ የሚለውን እንመልከት።

- ‹‹ማነው የሚኮንን ክርስቶስ የሱስ የሞተው ነውን ከሙታንም እንኳ የተነሳ በእግዚአብሔርም ቀኝ የተቀመጠ እርሱም ያስምረናል።» (ሮሜ. 8:34)
- «ስለዚህም ይቻለዋል ወደ እግዚአብሔር በርሱ የሚመጡትን ፈጽሞ ያድን ዘንድ ሁል ጊዜ ሀያው ነውና ጸሎት ስለ እርሳቸው ያሳርግ ዘንድ» (ዕብ. 7:25)
- «ልጆቼ ሆይ ይህችን ነገር እጽፍላቸዋለሁ ኃጢአት እንዳሰሩ ከላንትም ማንም ኃጢአት ቢሰራ ከአብ ዘንድ አማላጅ አለን የሱስ ክርስቶስ ጻድቅ» (1ኛ ዮሐ. 2:1) የቀድሞው መጽሐፍ የክርስቶስ አማላጅነት ዘመን አመጣሽ ሳይሆን የቀድሞ ቤተክርስቲያንና የቀደሙት አባቶች እምነት መሆኑን ነው የሚመሰክረው ይህን እውነት በቀድሞው መጽሐፍ ላይም ብቻ ሳይሆን አሁን በዘመናችን ያሉት መጻሕፍት ላይ በሚገባ የምናየው ነው። ለአብነት ጥቂቱን እናሳይዎት፡-

- «አስታራቂ ክርስቶስ በመላእክት ጌታ ፊት ቆሟልና» (ሔኖክ. 13:19) ይህን ያገኘነው በ1980 በታተመው በ81ዱ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሲሆን በተመሳሳይ አገላለጽ ለ11 ጊዜ የክርስቶስን አስታራቂነት ይነግረናል።
- «የአብ ሊቀ ካሕናት የሚሆን እርሱ የሰውን ባህሪ ከእግዚአብሔር ጋር አስታረቀ» (መጽሐፈ ቅዳሴ ስርዓተ ቅዳሴ ቁ.43፡ ገጽ 41)
- «በቅዱስ ደሙ ፈሳሽነት የአዲስ ኪዳን አስታራቂ ሆነ» (ውዳሴ ማርያም ዘአሁድ አንቀጽ አንድ)

- «ስለአመንበት በጎ ስራ ለመስራት የምንቀና ገንዘብ አደረገን ለእኛ ማልዷልና የምናምንበት ሊቀ ካህናት አለው።» (ሐይማኖተ አበው ዘዮሐንስ አፈወርቅ ክፍል ሁለት ምዕ 63 ቁጥር 26 ገፅ 224)
- «ስለ እኔ በቀራንዮ የፈሰሰ ንፁህ የሚሆን የመሲህም ደም እነሆ ስለ እኔ ይጮኻል ይህ የሚናገር ደም የእኔን የባርያህን ኃጢአት የሚያስተሰርይ ይሆን » (መጽሐፈ ቅደሴ ቅዳሴ ሐዋርያት ቁ.106 ገጽ 54).
- «ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ የእኔ ስለሆኑት ምህረትን ወደምለምንበት ወደ ሰማይ ወደ አባቴ አርጋለሁ አላቸው።» (መጽሐፈ ዚቅ ዘሰኔ ሚካኤል ገጽ 189)
- «አብ ሆይ ስለ ኢየሱስ እርዳን ክርስቶስ ወደ ቸር አባትህ አማፅነን የአብና የወልድ መንፈስ አጽናናን» (ሰዓታት ዘሌሊት ወዘነግህ በተስፋ ገ/ሥላሴ ማተሚያ ቤት የታተመ ስብሐተ ፍቁር ዘአምላክ ገጽ 222) (ምንጭ፡ - «የአዲስ ኪዳን መካከለኛ» መጽሐፍ)

እነዚህን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቋንቋዎች ስናይ በእርግጥ የቀድሞዋ ቤተክርስቲያን እምነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሆኑን እንረዳለን። ዘመናትን አልፋ የመጣችዋ ቤተክርስቲያን ይህንና ይህን መሰል በመልካም መሠረትነት ላይ የተገነባ እምነቷን በተለያዩ ጥቀርሻዎችና ጥላሸቶች እየተሸፈኑ ፊዕሞ የሌለና ቀድሞ የእርሷ ያልነበረ ያህል አሁን እየተቃወመችውና እያወገዘችው ትገኛለች። ስለዚህ ቤተክርስቲያን ራሷን እንድትፈትሽ እንጠይቃለን።



«እርሱ የአዲስ ኪዳን መካከለኛ ነው»

ዕብ 9:15

Scanned by CamScanner

ጎረቤቶቻችን ምን እያደረጉ ነው ?

በቅርቡ አንድ ጽሑፍ (8 ገጽ የሆነ የኮምፒዩተር ጽሑፍ ሆኖ በጣም ለብዙ ጊዜ ፎቶ ኮፒ እንደተደረገ ያስታውቃል) እጃችን ገባ።ጽሑፉ እከሌ አዘጋጀኝ ብሎ ባለቤቱን አይናገረም። ብቻ ርዕሱ (ስሙ) «ፍቅር ለእስማኤል ልጆች» ይላል። ውስጡ ግን አስገራሚ የሆነ ምስጢራዊ መረጃዎችን ይዟል።

ወረቀቱ የ2000 ዓ.ምን ዕቅድ ይዟል። ዕቅዱ «ክአባላት ውጪ በሌላ ተቃራኒ ኃይል» (እነርሱ «የሴቲቱ ልጅ» ይሉታል) እጅ እንዳይገባ በጥብቅ ያሳስባል። የዝግጅቱ ዋና አስተባባሪ ሺህ አህመድ ከማል ሲሆኑ ዋና ጽሕፈት ቤቱ (መገኛው) ሞምባሳ ኬኒያ ነው። ጽሑፍ ሁሉን ሲጨርስ «መልካም እድል» ይላል። ለምኑ? ለዕቅዱ።

ዝግጅቱ ከጷግሜ 1/1999 ይጀምርና የተለያዩ ነገሮችን እያዘዘ ነሐሴ 8-12/2000 ላይ ያበቃል። ዝርዝሩን በመጠኑ እየመረመርን በእርግጥም ጎረቤቶቻችን ምን እያደረጉ እንደሆነ እንይ።

የጷግሜ 1/1999 ዓ.ም እትድ ዝዋይ ሐይቅ ላይ ከቀኑ 6 ሰዓት እስከ 10 ሰዓት ድኪስ የሚከናወን ይሆናል። ለዚህ ዝግጅት ብቻ ሲባል ከውጭ የሚመጡ ት JOJO የተሰኙት ግለሰብ የዝግጅቱ መሪ ናቸው። ይህ ለአራት ሰዓታት የሚቆየው ልዩ ዝግጅት በሀገሪቱ ላይ (በኢትዮጵያ ላይ) የሚጸለይ ልዩ የድግምት የሚርት ዝግጅት ሲሆን የዝግጅቱ ርዕስ «ሞት» ይሰኛል። ሞት በኢትዮጵያ ላይ እንዲያንጎራብብ ከውጭ በመጡ ሰዎች ጭምር የሚታገዝ ልዩ የጸሎት ዝግጅት!

« ሌባው ሊሰርቅና ሊያርድ ሊያጠፋም እንጂ ስለሌላ አይመጣም» (ዮሐ. 10፡10) ያለውን የኢየሱስን ቃል የሰሙ ወገኖች ሁሉ ይህን የክፋት ተልዕኮ መነሻ ከማን እንደሆነ ያጡታል ብለን አንጠራጠርም!!ወደ ሌሎች ዝግጅቶች ደግሞ እስኪ እንሸጋገር መስከረም 18/2000 የሚከናወነው ቀጣዩ ዝግጅት ቦታው ደብረ ብርሃን ነው። የዝግጅቱ መሪ ፐርካጆ የተሰኙ ግለሰብ ናቸው አስተርጓሚ የሀገራችን ሰው (ኢትዮጵያዊ) የሆኑት ሺህ እንድሪስ አሊ ከሞያሌ ናቸው። የአሁኑ ዝግጅት መጠሪያ ስም ወይም የሚጸለይበት ርዕስ ደግሞ በሽታ በሀገሪቱ ላይ (በተሰይ በወጣቱ ላይ) እንዲመጣ ነው። እርስዎና ቤተሰብዎ በበሽታ እንዲጠቁና እንዲሰቃዩ ተጸልዮቦታል። ወገኖቼ መጤ ናቸው ማርያምን ከደዋታል የምንላቸው ክርስቲያን ወገኖቻችን ስለጤንነታችን እንጂ እንድንታመም

"ከእሾህ በለስ አይለቅሙም"

(ሉቃ 6÷44)

ጸልየው አያውቁም አስማኤላውያን ግን ይሔው እየጸለዩን ሳይሆን እየደገሙብን እየረገሙን ነው።

በዚህ ዕቅድ ላይ ዝዋይ፣ ደብረ ብርሃን፣ አዋሳ ፣አሰበ ተፈሪ ፣አዲስ አበባ፣ ናዝሬት ፣ከሚሴ ፣ሞያሌ፣ ባህርዳር ፣ደብረ ዘይት ዝግጅቱ የሚከናወንባቸው ከተማዎች ሲሆኑ ከሚጸለይባቸው ወይም በ2000 ዓ.ም በኢትዮጵያ ላይ እንዲደርሱ የሚፈለጉትና የታለሙት ግቦች ደግሞ ሞት ፣በሽታ፣ ዝሙት፣ ባዶነት ፣ቋንቋ መደባላለቅ፣ አለመግባባት ፣የጸሎት መልዕክት አለማግኘት ፣ግራ መጋባት፣ መቅበዝበዝ ፣በውስጣዊ እሳት መቃጠል (መፋጀት) ፣ ጭንገፋ ናቸው ። እያንዳንዱ የእርግማን ጸሎት ርእስ የሚጸለይበት ደግሞ የተለያዩ አካላት አሉ። ለምሳሌ በሽታ በወጣቶች ላይ፣ በውስጣዊ እሳት መቃጠል በአዳዲስ ባለትዳሮች ላይ፣ ጭንገፋ በወጣቱ ላይ (ጽሑፍ «አስፈሪ ኃይል» ሲል ነው ወጣቱን የሚጠራው) ባዶነት ጎልማሶች ላይ እንዲደርስ ነው።

ለዚህ ዝግጅት ከፍተኛ ገንዘብ መመደቡን የምናየው ዝግጅቱ የሚከናወንባቸው ስፍራዎችን ስናውቅ ነው። ከተማዎቹ ቀደም ሲል የጠቀስናቸው ሆነው የድግምት ጸሎቱ የሚደረገው ግን በዋቤ ሸበሌ ሆቴል ፣በመጋላ ሆቴል ፣በሳረስ አቦ ፣በሸራተን አዲስ፣ በባቡጋያ (ሆራ)፣በኦርጋን ባር ነው።

ከጥር 25 - 27 ለሁለት ቀናት በአዲስ አበባ ሳሪስ አቦ የተካሔደውን ዝግጅት መሪ የነበሩት ግለሰብ ስም 666 በሚል የተጠቀሰ መሆኑ በተለይ የዝግጅት ክፍላችንን ትኩረት ስቧል።

ውድ አንባቢ አሁንም ተኝተሃል? ጎረቤቶቻችን ግን በንቃት ላይ ብቻም አይደሉም ይህንንም እያደረጉ ነው። ጠላታችን ሰይጣን የዘመኑ ፍጻሜ እንደደረሰ አውቋልና በልዩ ትጋት ተነስቷል። ሐዋሪያው ጴጥሮስ «ንቁም ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንሚያገሣ አንበሳ ይዞራልና» (1ጴጥ 5:8) ሲል መክሮናልና ከመቼውም ጊዜ ይልቅ አሁን ልንነቃ የሚገባን አይመስሎትም?

በቁ. 1 እትማችን ላይ በሃይማኖታችን ላይ በግልጽ ዘመቻ እንደተጀመረ ተነጋግረን ነበር አሁን ደግሞ በስውር እየሆነ ያለውን በግልጽ አይተናል። ወንድሞቻችን የምንላቸው «ወንድሞቻችን» እንግዲህ ይህን ይመስላሉ። አንተ ግን ክርስቲያን ወገኔ የተሻለ ንቃትና የተሻለ ትጋት የሚጠበቅብህ እንደሆነ ቀደም ሲል የተናገርን ቢሆንም መድገሙ አግባብ ነውና ንቃና ትጋ እንልጋለን። ምክንያቱም ሰይጣን ከወዳጆቹ ጋር በተለየ መልክና በአስገራሚ ሁኔታ ውድቀታችንን እያበጀ ነውና ። እኔና እርስዎስ በተሻለ ሁኔታ መጸለይ የሚኖርብን አይመስሎትም?

ለሰው ቅን የምትመስል መንገድ አለች

ፍፃሜዋ ግን የሞት መንገድ ነው።

ምሳሌ 16÷25

Scanned by CamScanner

ጌቄል

"በሚዛን ተመዘንህ፣ ቀልለህም ተገኘህ" (ዳን.5:27)

የተሰኘችው ጽሁፍ ደርሰዎት ያወቃል?

መድሀኒታችን እየሱስ ክርስቶስ ስለመልካሙ ዘርና ስለእንክርዳድ በምሳሌ ባስተማረበት ወቅት እንዲህ ብሎን ነበር፦

"መንግስተ ሰማያት በእርሻው መልካም ዘርን የዘራ ሰውን ትመስላለች ሰዎች ሲተኙ ግን ጠላቱ መጣና በስንዴው መካከል እንክርዳድን ዘርቶ ሄደ።" (ማቴ13÷24-30)

መድህናችን የዘራውን መልካም ዘር በመቀበልና በማመን "ቀዳሚ ነን" የምንል እኛ እንደቀዳሚነታችን የተሰጠንን መልካም ዘር ነቅተን በመጠበቅ ፋንታ ስንተኛ "ጠላቱ" ተበሎ የተገለጠው የመልካም ዘር ባላጋራ ዲያቢሎስ እንክርዳድን ዘርቶ ይሄው መልካሙን ዘር እና እንክርዳዱን ለመለየት እስከምንቸገር ድረስ ሁሉን የራሳችን አድርገን ተቀምጠናል።

ጌቄል በተሰኘው አነስተኛ ጽሁፍ እነዚህን እንክርዳዶች ከስንዴው፡ ስንዴውን ከእንክርዳድ ለይቶ ለማሳየት የተነሳንበት ዓላማ ነው። የጽሁፉ ዓላማ በተለይ በቤተክርስቲያናችን ውስጥ ገነው የሚገኙትን በቅዱሳን ስም የመልካሙ ዘር ጠላት ያስገባውን ገድል፣ድርሳንና ተዓምር በሚል ስም የሚጠሩትን መጽሀፍ፡ መንፈሳዊነታቸውን በእግዚአብሄር ቃል መዝነን ከእግዚአብሄር ቃል ጋር ያልተስማሙትን በቻውን ትክክል ለሆነው ለመጽሀፍ ቅዱስ ስፍራ እንዲለቁ ለማድረግ ነው።

የማንንም ቅዱስ ክብር መንካት፡ የማንን ጻድቅ መልካምነት መጋፋት ፍላጎታችን አይደለም። መጽሀፍ ቅዱስም ቢሆን ይህን ማድረግ (የቅዱሳንን ክብር፡ መንካት) አይፈቅድም። ግን ቀደም ሲ ል እንዳልነው ነው። በዚህ ቅዱሳን ስም ሾልከው የገቡትን የስህተት አስተምሮዎች ወይም የመልካሙ ዘር ጠላት የዘራዉን እንክርዳድ ማሳየት እንደ መንፈሳዊ ሰውነታችንና እንደ አርቶዶክስ ነታችን ግዴታችን ነውና ይህን ነው የምናደርገው።

ለተጨማሪ ማብራርያ አልያም እርሰዎም የታዘቡትና የሚያካፍሉን ነገር ካለዎት ይጻፉልን።

ከጌቄል ዝግጅት ክፍል

የመ.ሣ.ቁ. 29783

አዲስ አበባ

ኢትዮጵያ

Mahabere Estifanos 29783

በሚዛን ተመዘንህ ፣ ቀልለህም ተገኘህ :: ዳን 5:27

ሐዋርያው ደመላሽ
የክርስቶስ ባሪያ
Hawoderos Demelash

Scanned by CamScanner